Date: Oct 19, 2013

# በእግዚአብሄር መደሰት(Enjoying God )

የሰው በምድር ላይ የመኖሩ አላማ እግዚአብሄርን ለማክበርና እና ከእርሱ ጋር በሚኖረው ህብረትም ደስታን ማግኘቱ ነው፡፡በእንግሊዝኛ ይህንን ሀሳብ የእግዚአብሄር ሰዎች እንዲህ ይገልጹታል፡-‹‹the chief end of man is to glorify God and to enjoy Him forever››እርሱን አምነንና ጌታችን አድርገን ወደ ጌታ በምህረት ከመጣን በኋላ አዘውትረን የምንገረምበት ነገር የሚጠብን ጸጋ ነው፡፡ይህ ጸጋ በሕይታችን እንደ እምነታችን ማጠን እያደገና እየጨመረ ይመጣል፡፡ጸጋው ደግሞ የእግዚአብሄር ህልውናን (His presence) ፍቅሩን በጎነቱን እና በረከቱን እንድንለማመድ ያደርገናል፡፡በክርስትና ህይወታችን ያለማቋረጥ ከእርሱ ጋር ህብረት እያደረግን ስንቀጥል ጌታን እየወደድነው እያስገረመንና እያስደነቀን ይመጣል፡፡በእርሱ መደሰትን የመሰለ ነገር እንደሌለም በሚባ እየተገነዘብን እንመጣለን፤መዝ 34፡8 ላይ ‹‹እግዚአብሄር ቸር እንደ ሆነ ቅመሱ እዩም››እንደሚል የመቅመሳችንና የማየታችን ልክ የመደሰታችንን ልክ ይወስነዋል፡፡

በዚህ አለም ከፍ ያለወና ተወዳዳሪ የሌለው ነገር በእግዚአብሄር መደሰት ነው፡፡ሰዎች በብዙ ነገር ደስታን ለማግኘት ይጥራሉ፡፡እነዚህ ደስታን ይሰጣሉ የሚባሉት ነገሮች ግን ዘለቄታዊ እርካታ ያለው ደስታ የሚሰጡ ሳይሆን ከሰአታት በኋላ እንደ ንፋስ የሚሄን ደስታን ነው የሚሰጡት፡፡ይህንን በራሴ ህይወት በሱስና በዝሙት አይቼዋለሁና መላምት አይደለም የምናገረው፡፡ለዚህ ነው በአይሁድ የዳስ በአል ማዝቂያ ላይ እየሱስ ‹‹ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣ››ብሎ የጮኸው፡፡ለብዙ ቀናት ሲጠግብና ሲንበሸበሽ የሰነበተን ሰው እንዲህ አይነት ግብዣ ማጠየቅ ቀልድ ነው የሚመስለው ነገር ግን እጅግ የሚገርም ማስረታዊ ጥያቄ እና ግብዣ ነበር፡፡ያ አይሁዶች የነበሩበት ግብዣ ስጋና ነፍስ ድረስ ሊደርስ የሚችል ጊዜያዊ ደስታን ፈጥሮ ሊሆን ይችላል ነገር ግን ወደ ወስጥ ዘልቆ በፍጹም ማረፊስን ሊያገኝ አይችልም፡፡ለዚህ ነው ደስታችን ሙሉ ሊሆን የማይችለው፤ለዚህም ነው ብዙ ጊዜ ከእንደዚህ አይነት ፈንጠዝያ ቦታዎች ደክሞን በባዶነት የምንመለሰው፡፡በእግዚአብሄር መደሰት ግን ወደር የለወም ለምን ቢባል መንፈሳችን ከመንፈሱ ጋር ህብረት በማድረጉ በሀይል ስለሚካ ዘለቄታ ያለወና እየጨመረ የሚሄድ ደስታ ነው፡፡ወደ ቤትም ስንመለስ እየዘመርንና እየተቀጣጠልን ነው የምንመለሰው፡፡አንዳንደም መተኛትም ላያምረን ይችላል፡፡

በእግዚአብሄር የመደሰታችን ማጠን እንደ መቀረባችን እንደ እምነታችን እና እርሱን እንደማወቃችን ይወሰናል፡፡አዎ በእግዚአብሄር እና በአግዚአብሄር ህልወና ወስጥ ሆኖ ለመደሰት እና ለመርካት እግዚአብሄርን ማወቅ ያስፈልጋል፡፡በተለይ ፍቅሩን መረዳት ይፈልጋል፡፡ኤፌ 3፡18-19 ላይ  ‹‹የእናንተ ስርና መሰረት በፍቅር ይጸና ዘንድ ከቅዱሳኑ ሁሉ ጋር ስፋቱና እርዝመቱ ከፍታወም ጥልቅነቱም ምን ያህል መሆኑን ለማስተዋል ከመታወቅም የሚያልፈውን የክርስቶስን ፍቅር ለማወቅ ትበረቱ ዘንድ››እንደሚል በእግዚአብሄር መገረማችንና መደሰታችን በማወቃችን ልክ እያደገ የሚሄድ እንደሆነ ልብ እንበል፡፡በዚሁ ቃል ላይ‹‹የክርስቶስን ፍቅር ለማወቅ›› የሚለው ሀሳብ በቀለም ደረጃ ስለሚታወቅ እውቀት ሳይሆን በጠለቀ ህብረት(deeper intimacy) ስለሚገኝ መረዳት፤መገለጥ እና ማወቅ ነው የሚናገረው፡፡ህብረታችን ደግሞ ከቃሉ ጋር በምናደርገው መጠበቅ እና በጸሎት በምናሳልፋቸው ጊዜዎች እየጠበቀ ይመጣል፡፡እንደዚህ ያለመታከት ስንገፋ ነው እያወቅነው፣እየተገለጠልን፤ መንፈሳዊወን አለም እየተረዳንና ለእኛ ያለወን የክርስቶስን ፍቅርና አላማ እያስተዋልን የምንመጣው፡፡

በመንፈሳዊው አለም መገለጥና መረዳት (revelation) ሁልጊዜ ደስታ (joy) አለው፡፡ይህንን መርህ ሁልጊዜ ልብ እንበል፡፡ጌታን ባወቅነው እና በተረዳነው ማጠን ደስታችን እየጨመረ ሲሄድ እምነታችን እያደገና እረፍታችን(እብ 4፡11) እየበዛ ይሄዳል፡-

- የጨመረ መረዳትና መገለጥ(INCREASED REVELATION)------------›የጨመረ ደስታ(INCREASED JOY)
- የጨመረ መረዳት(increased revelation) -------›በኢየሱስ ያለን እምነት ሚጨምር------›የደስታችን እና ሰላማችን መብዛት(ሮሜ 15፡13)
- ክርስቶስን በመንፈስ ማየት(SEEING CHRIST)-------------›የጨመረ መረዳት እናመደገፍ (INCREASED CONVICTION and MORE TRUST)----------->የጨመረ ደስታ

ሮሜ 15፡13 ላይ እምነት ወደ እግዚአብሄር ደስታ ወስጥ የሚከተን ቁልፍ ነገር እንደሆነ በግልጽ ተጽፏል፡፡እንዲህ ይነበባል፡-‹‹የተስፋ አምላክም በመንፈስ ቅዱስ ሀይል በተስፋ እንድትበዙ በማመናችሁ ደስታንና ሰላምን ሁሉ ይሙላባችሁ፡፡››ማመናችን  የደስታ እና የሰላም መንፈስ እንድንሞላ ዋና በር ነው፡፡ሮሜ 5፡2 ላይም ‹‹ወደ ቆምንበት ወደዚህ ጸጋ በእምነት መግባትን አግኝተናል››ይላል፡፡እምነትና ጸጋ አብረው የሚሄዱ ነገሮች ናቸው፡፡እምነትን የምናገኘወና እምነታችን የሚያድገው ደግሞ መንፈስ የሆነወን ቃል ስንሰማ ነው ቃሉ ‹‹እምነት ከመስማት ነው›› ይላልና ፡፡ስለዚህ በሚያያዝ እንዲህ ማስቀመጥ ይቻላል፡-

እምነት--------------------›ጸጋ------------›የእግዚአብሄር ህልወና-------------›ደስታ

ጠለት የሚቱጋው ከጌታ ጋር ያለን ህብረት ላይ ላዩን እንዲሆን እና ወደ ጠለቀ ነገር እንዳንሄድ በማዞከብ እና በሌሎች ነገሮች አእምሮአችንን እየከፋፈለ በሚቆት ነው፡፡እዚህ ጋ በሚስተዋል የምንወስደው እርምጃ እጅግ ይጠቅመናል ስለዚህ ጸንተንም የከፉን ሀሳብ በሀይል መቃወም አለብን፡፡እንዲህ የምላችሁ ለምን ማስላችሁ ብዙ ጊዜ በሚስተዋል ጸንቼ የጠለትን ስራ ሳፈርስ የሚደንቅ ነገር ወስጥ ጌታ ሲከተኝ ስላየሁኝ ነው፡፡በሚስተዋል የጠለትን ከበባ ለማሸነፍ ማንቃትና መዋጋት ይኖርብናል፡፡

ስለዚህ ምን እናድርግ በእግዚአብሄር ለመደሰት የሚለው ላይ አጭር ተግባራዊ ነገር አስቀምጬጽሁፌን እቋጫለሁ፡-

አንድ ነገር ብቻ ነው ማድረግ ያለብን ከጌታ ጋር በቂ ጊዜ ወስደን ህብረት እናድርግ፡፡ይህ ተግባራዊ እርምጃ ሲዘረዘር፡-

1.ከጌታ ጋር ተስማምተን ባልሄድንባቸው ነገሮችን ላይ ከምር የሆነ ጥልቅ ንስሀን እንግባ ብሎም በሚገባ እንማለስ፤እውነተኛ ንስሀ ያደሳልና ነው፡፡ይህንን እርምጃ ከወሰድን በኋላ ከሀጢያት ወቀሳ ለመውጣት በእምነት እንቁም(ጌታ መሀሪና ይቅር ባይ ነወና!)

2.ቃሉ ወስጣችንን እንዲለወጠወና ከላይ ወደ ተጠቀሰው አለም እንዲከተን እናጥናው፤እናሰላስለው ደግሞም እንተግብረው (ቃሉን መተግበር----------›አዲስ ማስተዋል(new insight)--------->ደስታ(joy)

3.ጠንከር ያሉ ጸሎቶችን እንጸልይ፤በጊዜወም አለጊዜወም ፊቱን እንፈልግ(ዋላ ወደ ወሀ ምንጭ እንደምትናፍቅ ነፍሴ አንተን ትናፍቃለች እንዳለ ዳዊት በጉጉትና በናፍቆት ፊቱን እንፈልግ)

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱትን ነገሮች በማድረግ ብዙ መጽናናትን፣ደስታን ፣እረፍትን እና በረከትን አግኝቻለሁ፡፡ጌታን በሚደሰስ ሜሌኩ ስላየሁት በቂ ህያው ምስክር ነኝና በሚገባ እንድትተጉና ጌታን እንድታዩት አደፋፍራችኋለሁ፡፡እርሱ ታማኝ ነው፤እርሱን የሚመስል የለም ስለዚህ ኑና በህልወናው ወስጥ እረፉ!!

በቀለ በላቸው(ዶ/ር)